# ኦሮሞ ማመስገን ካለበት ሊያመሰግን የሚገባው እኔን እንጅ አነ ጃዋርን አይደለም!!!

በዘመነ ወያኔ እነ ኦነግ፣ እነ ጃዋርና ሌሎች ኦሮሞን እንወክላለን የሚሉ ድርጅቶች የኦሮሞን ሕዝብ ከሌላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ነጥለው በወያኔ ላይ እንዲነሣ ሲቀሰቅሱ ሲያነሣሡ ቢኖሩም የኦሮሞ ወጣቶችን በኦነግ እያስጠረጠሩ እስር ቤቱን ሁሉ በኦሮሞ ወጣቶች እንዲሞላ ከማድረግ በስተቀር እስከ ሚያዚያ 11,2006 ዓ.ም. ድረስ ኦሮሞ "ጥቅሜ ተነካብኝ!" ብሎ በመነሣት ያስመዘገበው የዐመፅ ታሪክ አልነበረም!

ዕድሜ ለእኔ ይበሉና መጋቢት ወር 2006 ዓ.ም. ላይ በዕንቁ መጽሔት የአኖሌ ሐውልት ሊመረቅ አካባቢ በሐሰተኛ ታሪክ ላይ ተመሥርቶ በዛሬው ጠ/ሚ ዐቢይ አሕመድ አስፈጻሚነትና ክትትል የተገነባውን የአኖሌን የጥፋት ሐውልትና ተያያዥ ጉዳዮችን በተመለከተ የጻፍኩት ከታች ሊንኩን (ይዞን) ያያያዝኩላቹህን ጽሑፍ በጻፍኩ ጊዜ ግን ታሪክ ተቀየረ፡፡

[***http://www.goolgule.com/monuments-for-martyrs-or-victims/***](http://www.goolgule.com/monuments-for-martyrs-or-victims/)

ጽሑፉ በትክክለኛ ታሪክ ላይ ተመሥርቶ የተጻፈ ፖለቲካዊ (እምነተ አሥተዳደራዊ) ቢሆንም ኦሮሞ ነኝ የሚሉትንና በጠባብ ብሔርተኝነት የሰከሩትን ሁሉ አሳበደ፡፡ አሳብዶ አልቀረም ዐመፅ ቀስቅሶ አደባባይ አስወጣ፡፡

ዐመፁ መጀመሪያ ላይ የት ተቀሰቀሰ መሰላቹህ በጅማ ዩኒቨርስቲ ሚያዚያ 11,2006 ዓ.ም. ተቀሰቀሰ፡፡ ከዚህ ቀን አስቀድመው ተማሪዎቹ የዩኒቨርስቲውን (የመካነ ትምህርቱን) አሥተዳደር እኔንና የዕንቁ መጽሔትን አዘጋጅ ለፍርድ እንዲያቀርብ፣ በዩኒቨርሲቲው ያለው መጽሔቱ ተሰብስቦ እንዲቃጠል እንዲያደርግ አከታትለው ጠይቀው ስለነበርና ምንም እንኳ ካመፁ በኋላ በጥያቄያቸው መሠረት በጅማ ዩኒቨርሲቲና በዐቃቤ ሕግ ከሳሽነት እኔና የመጽሔቱ አዘጋጅ ሐሳብን የመግለጽ መብታችን ተገፎና እንደ ወንጀል ተቆጥሮ ብንታሰርም በወቅቱ ግን ይህ ጥያቄያቸው ተፈጻሚ ያልተደረገ ስለነበረ የዩኒቨርስቲው ተማሪዎች ሚያዚያ 11, 2006 ዓ.ም. ዐመፅ ቀስቅሰው ንብረት አወደሙ፣ የእጅ ፈንጅ አፈንድተው የሙትና የቁስለኛ ጉዳት አደረሱ፣ ለሳምንታት የመማር ማስተማርን ሒደት አስተጓጎሉ፡፡

ዐመፁም በጅማ ዩኒቨርሲቲ ሳይወሰን ተማሪዎቹ ኦሮሚያ በሚሉት የሀገራችን ክፍል ባሉ ዩኒቨርስቲዎች እየተደዋወሉ በሌሎቹም ዩኒቨርስቲዎች እንዲቀጣጠል አደረጉ፡፡ ቀጥሎም ወደ ሃይ ስኩሎች (ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች) እንዲሸጋገር አደረጉ፡፡ ዐመፁ እየሰፋ ሲሔድ እኔንና የዕንቁ መጽሔትን ለፍርድ እንድንቀርብ የሚለውን ጥያቄ ትተው የአዲስ አበባን የማስፋፊያ አቅድ (Master plan) ወደ መቃወም ወሰዱትና አገሩን ቀውጢ አደረጉት፡፡ በዐመፁ ድንጋይ በመወርወር ንብረት በማውደም ተወስነው ሲያምፁና ዋጋ ሲከፍሉ ከዓመት በላይ የቆዩ ቢሆኑም ወያኔ ለይስሙላ የአዲስ አበባን ማስፋፊያ አቅድ እንደተወው እንዲገልጽ ከማድረግ ባለፈ ምንም ነገር መለወጥ አልቻሉም ነበረ፡፡ የወልቃይት የአማራ ማንነት እንቅስቃቄ ተወካይ ኮሎኔል ደመቀ እራሱን ለመከላከል በወያኔ አፋኝ ኃይል ላይ በወሰደው አስደናቂ እርምጃ ዐሥራ ምናምኑን ወያኔ ደፍቶ የወያኔን ቀልብ በመግፈፍ አማራ ብዙ ዋጋ ወደ ከፈለበትና ድንጋይ በመወርወር ሳይሆን የአገዛዙን አካላት እስከመግደል የደረሰ እርምጃ በመውሰድ ዐመፅን ሲቀላቀል ግን ነገር ተለውጦ ያችን የኔን ጽሑፍ እግዚአብሔር ለበጎ አደረገውና በኦሮሞና በአማራ የጥምረት ዐመፅ ይሄው ለዚህ ልንበቃ ቻልን፡፡

ልብ በሉ ወያኔ ተሸንፎ ለይቶለታል አላልኩም፡፡ ነገር ግን መላ ጠፍቶበት የሚያደርገውን አጥቶ የተሸነፈና እጅ የሰጠ ላስመሰለ ትወና፣ በቦታው ኦሕዴድን በማስቀመጥ ወደ ሞግዚት አሥተዳዳሪነት ለመውረድ፣ እስረኛ ለመፍታት፣ ጥገናዊ

ለውጥ ለማድረግ.... ግን ተገዷል ነው እያልኩ ያለሁት፡፡ ይሄም ትልቅ ድል ነው ግን አስተማማኝ አይደለም፡፡ ድሉ ተመልሶ እንዳይቀለበስ አድፍጦ ያለውን የጥፋት ኃይል አጠናቆ ማክሰም የግድ ያስፈልጋል፡፡

እናም አሁን ለደረስንበት ስኬት ኦሮሞ ማመስገን ካለበት እኔን ዋናውን አቀጣጣዩን (The igniter) ነው እንጅ እሳቱ ከተጫረና ከተቀጣጠለ በኋላ እፍ እያለ ያያዘውን አይደለም! ውለታ ቢስ አትሁኑ!!! ኦሮሞን ብቻ አይደለም እየወቀስኩ ያለሁት ሁሉንም የኢትዮጵያ ሕዝብ ጭምር እንጅ፡፡

የሚያሳዝነው እነኝህ "ኦሮሞን እንወክላለን ዐመፁን መርተን ለዚህ ያደረስን እኛነን!" የሚሉ የኦሮሞ አክቲቪስቶች (ሥሉጣን) እና የተለያዩ አካላት ግን አውቀው ይሁን ሳያውቁ አላውቅም ይሄንን ድል የራሳቸው ብቻ አድርገው በማሰብ ወያኔ "ዋጋ ከፍያለው!" እያለ የአማራን መሬትና የሀገሪቱን ሀብት እንደዘረፈው ሁሉ እነሱም "ዋጋ ከፍለን ለዚህ ድል ያበቃን እኛ ነን!" በሚል ለራሳቸው ዋጋ በመስፈር ኦሮሞ ወደ ኢትዮጵያ ሲገባ በወረራ የወሰደው የአማራ ሀገር ሳይበቃው አሁንም የቀረውን የአማራ መሬት ለመንጠቅ ኦሮሚያ የሚሉት ሕገ ወጥ ካርታ (ትልመ ምድር) አውጥተው በመቀስቀስ ላይ ይገኛሉ፡፡

የአማራ ሕዝብ ይሄንን ጠንቀኛና ቀማኛ አስተሳሰብ ብዙ ስር ሳይሰድ የተለያዩ አማራጮችን በመጠቀም ከሰዎቹ አእምሮ ለማስወገድ ጊዜ ማጥፋት የለበትም፡፡ በዚያም በዚህም ብለህ እነዚህን እፍረተቢስ ግለሰቦች የኦሮሞን ሕዝብ እየመረዘ ካለው ፈጽሞ አግባብነት ከሌለው ጥያቄና እንቅስቃሴያቸው እንዲታረሙ ማድረግ ይጠበቅብሃል፡፡

እነኝህ ግለሰቦችና አካላት ከአማራ ሕዝብ ፊት ሲቀርቡ ኢትዮጵያዊነትንና አንድነትን እናምንበታለን፣ እንፈልገዋለን፣ እንታገልለታለን ብለው አጣፍጠው እያወሩና አስፈላጊነቱንም እየገለጹ ባለበት ሁኔታ "ሕዝባችን!" ከሚሉት ከኦሮሞ ሕዝብ ፊት ሲቀርቡ ግን ተመልሰው ወርደውና ጠበው እንደገና "ድንበርህ እዚያ ድረስ መሆን አለበት! ይሄንን ሳታደርግ እንቅልፍ እንዳትተኛ!" እያሉ የኦሮሞን ሕዝብ ዝርፊያ የሚሰብኩ፣ ጠባብና ጽንፈኛ ብሔርተኝነትን የሚቀሰቅሱና ሕዝብ የሚመርዙ ከሆነ በአጸፋ እርምጃ ጥቅማችንን ለማስከበር ከመዘጋጀት በስተቀር ከነሱ ጋር የቅጽበት ጊዜ ልናባክን አይገባም!!! የልጆች ጨዋታ ነውና ምን ጥቅም አለው???

አማራ ሆይ! ይሄን ነገር በቸልታ ተመልክተን ካለፍነው አትጠራጠሩ በቅርቡ ቁምስቅልህን የምታይበት ይሆናል፡፡ አማራ በታሪኩ መሬትን "የኔ!" ብሎ አያውቅም፡፡ አሁን ግን እንደምታዩት "የኔ!" ለማለት ተገዷል፡፡ "የኔ" ለማለት የተገደደው በግራና በቀኝ መሬቱን እየተናጠቁ "የኛ ነው!" የሚሉ ዘራፊዎች ስለመጡበት እንጅ "የኔ የብቻየ!" የሚለው መሬት እንዲኖረው ስለፈለገ አይደለም እንዲህ ዓይነት ጠባብ አስተሳሰብም ኖሮት አያውቅም፡፡ ለዛም ነው በግራና በቀኝ በላይና በታች መሬቱ በወራሪና በስደተኛ ተወስዶበት እያለና ዛሬ ባይሆንም ጉልበት በነበረውና የፈለገውን ማድረግ ይችል በነበረበት በቀደመው ዘመን በተለያዩ አጋጣሚዎች የተወሰደበትን መሬት ወይም ሀገር መልሶ የራሱ ማድረግ እየቻለ ሳያደርገው ሊቀር የቻለው፡፡

ይሄ እጅግ የበዛ የአማራ ሆደሰፊነት ግን ሀገር የማያውቁና ያልሠለጠኑ መሠልጠንም የማይችሉ ጠባቦችን፣ ማሰብ ማገናዘብ የማይችሉ ቀማኞችን፣ እፍረት ፈጽሞ የማይሰማቸውንና ይሉኝታ ቢስ ዘራፊዎችን ደጋግሞ እያሳሳተ መሬቱን እንዲቀራመቱት አድርጓል፡፡ እንግዲህ በዚህ በሠለጠነ 21ኛው መቶ ክፍለ ዘመንም ዓይን ባወጣ እፍተረተቢስነትና ይሉኝታቢስነት እንዲህ መታሰቡ ካልቀረ አማራ በየጊዜው ሀገሩን ለእንግዳና ለስደተኛ እየሰጠ እያስረከበ ሀገር አልባ ሆኖ ሊቀመጥ አይችልምና ወደኋላ ተመልሶ መሬቱን ከመሰዱ አካላት ጋር ለመተሳሰብ እንደሚገደድ እነኝህ የተለያዩ በላይና በታች ያሉ ቀማኞቹ ማሰብ ይኖርባቸዋል፡፡ በዚህ ሒደትም ይህች ሀገርና ሕዝቧ ዘለዓለማቸውን በእርስበእርስ ግጭት እንደቆረቆዘን መኖር ይሆናል፡፡ እነ ጃዋርና እነ የትግሬ ልኂቃን እራሳቸውን እንደተማረና እንደሠለጠነ ሰው የሚቆጥሩ ከሆኑና የሠለጠኑ የተማሩ ከሆኑ ይሄንን እጣፈንታ ሊመርጡ አይችሉም ብየ አስባለሁ፡፡ ስለሆነም እንደተማረ እንደሠለጠነ

ሰው ተረጋግተው ያስቡበት፡፡ ካልሆነና በጨለማ ዘመን አስተሳሰብ ታንቀው ኦሮሚያ ኦሮሚያ ትግራይ ትግራይ እያሉ የሚገፉ ከሆነ ግን ሁሉም ዜጋ ዕኩል የሚታዩባትና ዕኩል ተጠቃሚ የሚሆኑባት ዲሞክራሲያዊት (መስፍነ ሕዝባዊት) ሀገርን የመፍጠሪያውን ይሄንን ዕድል በሚያሳዝን ሁኔታ ማምከናቸውንና ሽግግሩ ወደጨለማ ዘመን ማድረጋቸውን ይወቁት፡፡

ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!! ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር!!!

ሠዓሊ አምሳሉ ገ/ኪዳን አርጋው

amsalugkidan@gmail.com